# ዜና አመዝኤ





## በዚህ ዕትም ውስጥ

የሶማሌ ክልል የሰብዓዊ ዕርዳታ እንቅስቃሴ ከመቼውም ጊዜ የተሻለ እንደሆነ ተገለፀ።
*ገጽ 3*

በሶማሌ ክልል አስጊ ደረጃ ላይ የደረሰ የህፃናት የምግብ እጥረት አልተከሰተም።
*ገጽ 4*

ብሔራዊ የአደጋ ሥራ አመራር ፖሊሲ ማሻሻያ ላይ የምክክር አውደጥናት ተካሄደ።
*ገጽ 5*

ኤች አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከል ሁሉም ወገን አስፈላጊውን ግንዛቤ ሊጨብጥ እንደሚገባ ተገለፀ።
*ገጽ 6*

የመኸር ቅድመ አዝመራንና የአርብቶ አደር አካባቢዎችን ሁኔታ የሚያጠኑ ቡድኖች ተሰማሩ።
*ገጽ 7*

በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ
ስልክ. 5529259
ፖ.ሳ.ቁ 5686
ድረገጽ፣ www.dppc.gov.et

## ለሱማሌ ክልል ከ 124 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተጓጓዟል

**✦ ሰብዓዊ ዕርዳታው ሊደርስ ለሚገባቸው ወገኖች ብቻ እንዲውል አስተማማኝ የቁጥጥር ስልቶች መዘርጋታቸው ተገለፀ**

በሱማሌ ክልል አምስት ዞኖች ለሚገኙ ሰብዓዊ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ካለፈው ጥቅምት ወር አጋማሽ ጀምሮ እስከ ህዳር ወር መጨረሻ ባለው ጊዜ ውስጥ በጠቅላላው 124 ሽህ 175.8 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ የተጓጓዘ መሆኑ ታውቋል።

ዕርዳታውን የማጓጓዙ ሥራ ከተጀመረበት ጥቅምት 19 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ የምግብ ዕርዳታውን በክልሉ ያለው ወቅታዊ ዝናብ ሊያሳድር የሚችለውን ተፅዕኖ ከግምት በማስገባት ለማጓጓዝ ሥራ ቅድሚያ በተሰጠባቸው ፊቅ ፣ ጎዴ ፣ ቆራሔ፣ ደገሀቡር እና ዋርዴር ዞኖች ለሚገኙ 641 ሺህ 970 ሰብዓዊ ዕርዳታ ፈላጊዎች ከተመደበው 198 ሺህ 595 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ውስጥ እስከ ህዳር ወር 2000 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ ባለው ጊዜ በ 453



የጭነት ተሽከርካሪዎች 124 ሺህ 175.8 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ በአደጋ መከላከልና ዝግጅነት ኤጀንሲ ከድሬዳዋ ማዕከላዊ መጋዘን የተጓጓዘ መሆኑን የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ።

ከዚሁ ለአምስቱ ዞኖች ከተጓጓዘው ጠቅላላ የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 14 ሺህ 999.43 ኩንታል ለፊቅ ፣ 26 ሺህ 746.44 ኩንታል ለጎዴ 24 ሺህ 916.96 ኩንታል ለቆራሔ ፣ 28 ሺህ 115.11 ኩንታል ለደገሀቡር እና 29 ሺህ 397.82 ኩንታል ለዋርዴር የተጓጓዘ ሲሆን ይኸም ለዞኖቹ ከተመደበው ጠቅላላ የምግብ ዕርዳታ 63 በመቶ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል። ቀደም ባሉት ዓመታት ይህን ያህል መጠን ያለው ሰብዓዊ ዕርዳታ ለማጓጓዝ ከ2 እስከ 3 ወራት ይፈጅ እንደነበርና አሁን በአንድ ወር ጊዜ ወስጥ የተመዘገበው ውጤት በክልሉ ከመቸውም ጊዜ የተሻለ መረጋጋት መኖሩንና የተቀናጀ የማስተባበር ሥራ መከናወኑን የሚያመለክት እንደሆነም ዋና ዳይሬክተር ሲሞን መቻለ ለሀገር ውስጥ ጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ አብራርተዋል።

ዜና አመዝኤ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲና ተባባሪዎቹ የሚያካሂዷቸውን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እንቅስቃሴዎችንና ሌሎች ተጊዳኝ ተግባራትን የሚዘግብ ወርሃዊ ልሳን ነው